በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት አደረጃጀት ዘርፍ ምርጥ ተሞክሮ

ሐምሌ/2016ዓ/ም

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ



መግቢያ

የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 በልጽግና ፓርቲ ሴት ሊግ ጽ/ቤት በዋናነት በፓርቲው ውስጥ ያሉትን የፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ሁሉም በየደረጃው ያሉ ህዋሳትና መሰረታዊ ድርጅቶችን በሁሉም አደረጃጀቶች በማሰባጠር ለሀገር የሚበጅ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እነዚህ ስራዎችን ተግብሮ ውጤታማ ለማድረግ መግባባት ላይ የተመሰረተ የድርጅታችን መርህን በመከተል ሁሉም ተቀራራቢ ዉጤት እንዲያመጣ ለማድረግ ደረጃቸውን ለማሻሻልም ካሉበት በመነሳት ለውጦችእንዲታዩ ጥረት በየጊዜው ይደረጋል፡፡ በህዋሳት ደረጃ ስናየው ደግሞ አስተባብሮና አቀናጅቶ የአካባቢውን ህብረተሰብበ መጥቀም፤ አካባቢን በመጠበቅ የተሻሉ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በዚህም አመርቂው ጤቶች ስለተከናወኑ ምርጥ ተሞክሮውን ለመቀመር የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶች ተጠናቀው ለዚህ በቅቷል፡፡

ዓላማ

በፓርቲያችን ውስጥ የሚተገበሩ ስራዎች ሁሉን አቀፍ የሆኑና ሰውኛ ላይ ያተኮሩትን በይበልጥ ደግሞ በህዋስ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ለሌላው ህዋስ እንዲጠቅም ማስቻል ነው፡፡

ተሞክሮው የቀረበባቸው መንገዶች

ተሞክሮ 1.ከመዋቅሩ የአስተሳሰብ ጥራት እና የአስተሳሰብ ግንባታ ስራችን አንፃር

- የፓርቲዉን ፕሮግራም መግዛት እሳቤዎችን የራስ በማድረግ እሴት የመጨመር እና በፓርቲዉ ላይ ያላቸዉን እምነት እንዲጎለብቱ ከመገቃዝ አንፃር በሴት ሊግ ህዋሳት ስለፓርቲዉ እሳቤ እና ራዕይ በዝርዝር መናገር የሚችሉ አባላት በተጨባጭ ማየት መቻሉ
- የፓርቲያችን አጀንዳዎችና ዕቅዶች በዉጤታማነት እንዲፈፀሙ አመራሩና አባላቱ ያለዉ ተሳትፎ አንፃር በሁሉም ደረጃ በሚባል መልኩ ያላቸዉ ተሳትፎ በግልፅ የታየበት /ለአብነት በሰላም እና ፀጥታ ስራ;በበጎ ፍቃድ ተግባራት; በመልካም አስተዳደር ; በከተማ ግብርና እና በሌማት ቱርፋት
- ፓርቲዉ ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ሙህራን ሴቶችና ወጣቶች ላይ ያተኮረ ምልመላ ማድረጉን በህዋሶች እራሳቸዉን ለማብዛት የአባላት ምልመላ ስራ ዋና ተግባር አርገዉ በመስራታቸዉ በአንድ ህዋስ ተጨማሪ ልላ ህዋስ መመስረት ስራ ከሃይል ማሰባሰብ ግብ አንፃር በተጨባጭ የታየ መሆኑ

ተሞክሮ 2. በስራ እድል ፈጠራ በ መለየት ተደራጅተው ወደ ስራ ከገቡ አንፃር

- በተለያየ የስራ ዘርፍ ተደራጅተው ስራ ላይ ያሉ አባላት፡- 100
- በህዋሳት ደረጃ በጓሮ አትክልትምና በዶሮ ተደራጅተው ስራ ላይ ያሉ 4 ህዋስ ሲሆኑ ሌላው በራስ ተነሳሽነት ሰርተው ሞዴል የሆኑ ናቸው ከመ/ድርጅት ጋር በተያያዘ በራሳቸው ወደ ስራ ገብተው ለሌላውም እርዓያ በመሆን የተለያየ ለውጥ ያመጡና ከራሳቸውም ተርፈው በሰንዴ ማርኬት ማቅረብና ወደ ስራ የገቡበት አግባብ ነው ያለው፡፡


የከተማ ግብርና በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የአየር አምባ
የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት
Infinix
Infinix




WORLD
FIBERGLASS



የተገኙ ውጤቶች

- የመጡ ለውጦች በጣም ዘርፈ ብዙና የተሻለ አስራር የሚታይበት እንዲሁም በህዋስም ደረጃ በምንወያይበት ወቅት ምርጥ ተሞክሮዋቸውን እያሰፉ እየተሰራና ከራስ ተርፎ ለሌላም አቅርቦት በማቅረብ የተሻሉ ስራዎችና ውጤቶች መቷል።

 





- **ተሞክሮ 3**. በህዋስ ቁጠባ በመቆጠብ በመበዳደር የስራ እድል ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ሞዴሎች

- ✓ በቆጠቡት ብር ስራ እድል ፈጥሮ ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር ይቀረናል ነገር ግን አሁን ላይ በዛ መንገድ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራ ንቅናቄ የመስራት ሂደት ላይ ነን ነገር ግን የሚታዩ ውጤቶች አሉ


World
Environment Day
adidas




የተገኙው ጤቶች

- በብልፅግ ና እሳቤ ውስጥ በመሆን በቆጠቡት ብር የተቸገረን መርዳት
- በህዋሳቸው ውስጥ ችግር ወይም ሀዘን የደረሰባትን ሴት መጠየቅና የመደጋገፍ ስራ ይሰሩበታል
- የንቅናቄ ተግባርም ያከናውኑበታል ለምሳሌ፡- ቦንድ ግዢ
- ለበዓላት የማእድ ማጋራት ስራን በተባበረ ክንድ ይሸፉንበታል
- በህዋሷ ውስጥ በመደራጀት ማህበራዊ፤ ፖሊቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ማቃለል ተችሏል
- የአባላት መዋጮ፣የአባላት ምልመላ ስራ በተገቢው መንገድ ያከናውናሉ

በተሻለ መልኩ የሚንቀሳቀሱ ህዋሶች በቁጠባው ዘርፍ

- ✓ ኦሎፒያ ህዋስ
- ✓ ብርሀን ህዋስ
- ✓ ብርሸዋ ቁ-1 ና ቁ-2
- ✓ ወይራ ሰፈር ህዋስ
- ✓ ሰላም ሰፈር ሀዋስ

ተሞክሮ 5 .በበጎ ስራዎች በመሳተፍ የተሰሩ ቤት እድሳት ፤ማእድ ማጋራት፤ደም ልገሳ እና ሌሎች ተግባራት በዝርዝር በሊጉ የተሰሩ ይገለፁ

- በራስ ተነሳሽነት የአቅመ ደካማ ቤት ማደስ፣
- በአላት ሲደርሱ ስራዎችን የጋራ በማድረግ ምንም ለሌላቸው አቅመ ደካማ ቤት ለቤት በመሄድ ማእድ ማጋራት ስራ መስራት፣
- ወላጅ አልባ ለሆኑ ልጆች የት/ት ቁሳቁስ መሰብሰብ፣አልባሳት መስጠት ወ.ዘ.ተ
- እንዲሁም በቅርቡ ለትግራይ ክልል መልሶ ማቋቋም የተሻለ ድጋፍ በማድረግ መሳተፍ መቻላቸው
- ደሜን ለወገኔ በማለትም ያለ ምንም ቅሬታ በበቂ ሁኔታ መሳተፍ መቻላቸው

  ለትግራይ ክልል መልሶ ማቋቋም በመሰባሰብ ላይ





ደም ልገሳ





የአቅመ ደካማ ቤት እድሳት





የክረምት ስራዎቻችን ከጉድጓድ ቁፋሮ እስከ ችግኝ ተከላ በስራ ላይ




የበጋ በጎ ፍቃድ ችግኝ እንክብካቤ






ተሞክሮ 6. በሰላም ሰራዊት እና በሌሎች የአካባቢ ልማት ስራዎች እንደ ምሳሌ በህዋስ የተሰሩ በሊግ አባላት የተሰሩ ስራዎች በዝርዝር በህዋሷ ስም ጭምር ይገለፁ

- ✓ አካባቢን በንቃት በመጠበቅ ስራዎችን በብቃት መወጣት
- ✓ አዳዲስ ሰላም ሰራዊት መመልመል

ሰላም ሰራዊት ስምሪት



ጽዳት ዘመቻ





የቡድን(የህዋስ) ውይይትማከናወን

ህዋስ ውይይት የፓርቲያችን ህገ-ደንብ በሚያዘው መሰረት በወር 1 ጊዜ አካባቢያዊ ሁኔታቸውን መሰረት ባደረገመልኩ ይወያያሉ፡፡ በዚህም በርካታ አካባቢያዊ የሆኑ ማህበራዊ ችግሮች ተፈተዋል፡፡ ብልፅግና ሰውኛ መሆኑን ለማስገንዘብ ጊዜውን ያማከሉ ውይይቶች ተከናውነዋል፡፡ ስለሆነም በህዋስ ውይይት ላይ ችግር ፈቺ የሆኑ ነገሮችን በማከናወን ካላቸው ላይ ቁጠባን በመቆጠብ፤ ርስበርስ በመረዳዳት ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲሁም ህዋሷ በአካባቢያዋ ያሉትን ለጋሽ ሰዎችን በማናገር ግንባር ቀደም በመሆን የተቸገሩ ወገኖቻችን እንዲረዱ ማድረግ የተደረገበት ሂደት የተሻለነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ምልከታ ማድረግ

በዚህ ህዋስ አማካኝት በሚቆጥቡት ብር የቤት ኪራይ መክፈል ያልቻለችን አባል ከቁጠባቸዉ በመዉሰድ ወደ ጎዳና ከመዉጣት ታድገዋል እና ከዚህ በተጨማሪ በራሳቸው አካባቢያቸዉ ላይ የወለድችን ሴት ሀዘን የገጠመዉ ካለ ከቁጠባቸዉ በመዉሰድ ማህበራዊ ሃላፊነታቸዉ ሲወጡ የታበት ሁኒታ ሌላዉ ተሞክሮመሆንየሚችልነዉሌላዉለህዳሴቦንድግዢበህዋስአማካኝነትበስጦታ፡ መልክገቢተደርጋል

ቃለ-መጠይቅ ማከናወን

በህዋሷ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ስራዎች ተጠርንፈው መጓዝ ስለሚያስፈልጋቸው ከህዋስ ሰብሳቢው በመነሳት ተግባራቶቹን መሰረት ያደረገ ቃለመጠይቅ የተከናወነ ሲሆን ለሌላው ተሞክሮ መሆን በሚችልበት ሁኔታ ማስቀመጥ መቻሉ የተሻለ ነው፡፡ ሁሉንም የህወሱን አባል ጠርንፎ መጓዝ፤ ራሱ የህዋሱ አባል ጠንክሮ ሌላ ህዋስ መመስረት የቻለበት ርቀት ለብልፅግናችን ጥሩ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ሞዴሌ ህዋስ ውይይቶች ስራዎች በፎቶ









- በሙዳይ ንቅናቄ ስራችን ላይ የታዩ በህዋት ሞዴል የሆኑ ተግባራት ከስም ስያሜ እና አባላት ምመላ ስራ እና ከውስጠ ፓርቲ ስራዎች እንደ ወረዳችሁ ነባራዊ ሁኔታ በዝርዝር ይቀመጥ፡፡
    - እንደ ወረዳችን ነባራዊ ሁኔታ ሞዴል ህዋሳት ሁሉም ስም ስያሜ አላቸው ሆኖም ያ ስም ስያሜ የሚወጣው አንድ ላይ በጋራ በመናበብና በቅንጅት በመፍጠር በውይይቶች ወቅት በተሌ ሁኔታ በማፅደቅ በቃለ-ጉባኤ ገቢ ያደርጋሉ
    - ሌላው ባሉበት ቀጠናና ብሎክ ደግሞ አዳዲስ አባላትን በመመልመል ወርሀዊ ክፍያንም በዛው በመቀበል ማጠናከር፣ መደገፍ ፣ህዋስ ውይይት ላይም እንዲገኙ ድጋፍ ክትትል የማድረግ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡
    - ባጠቃላይ ደጋፊ አመራሮችን ሳይተብቁ ያለምንም መንጠባጠብ ህዋስ ውይይቶችን ማድረግ መቻላቸውና የሙዳይ ንቅናቅንም የማስቀጠል ስራ ይሰራሉ፡፡

ክፍል ሁለት

አጠቃላይ ገፅታ

መነሻ ሁኔታ

ከቅድመ ስራው በፊት የተሰራ ስራ

ይህ ምርጥ ተሞክሮ በሚዘጋጅበት ወቅት በፓርቲ ውስጥ የሚሰሩ የተለያዩ ተግባራቶች መሰረት ያደረገ ሲሆን ያጋጠሙ ችግሮች፤ደካማ ጎኖችን መሰረት በማድረግ ለችግሩ መፍትሄ ሊሆን የሚችለውን አሰራር መቀመር እንደሚያስፈልግ መግባባት ላይ መድረስ የመጀመሪያው መነሻ ሆኗል፡፡ በዚህም በዋነኝነት በህዋሷ ውስጥ የሚከናወኑ ማህበራዊ ችግሮችን ለማገዝና ለመፍታት የሚደረገው ጥረት ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዝውውር

በማድረግ እና የምስል መረጃዎችን በመያዝ ሊደረግ የሚገባውን ቅድመ ሁኔታ እንዲያሟላ ጥረት ተደርጓል፡፡

የነበሩ ምቹ ሁኔታዎች እንደ መነሻ

ብልፅግና ፓርቲ ሰውኛ ነው ስንል በተግባር መገለፅ ከጀመር ሰንበትበት ብሏል፡፡ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ያለውን በማካፈል የተቸገሩትን በመርዳት፤የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስና የተለያዩ መሰል ስራዎችን በመስራት ለውጥ እንዲመጣ ያደረገ ሲሆን በህዋሱ ውስጥም ይህን መሰልነገሮች እንደመነሻ ጠቅመዋል፡፡ ፓለቲካዊ እሳቤዎች ከፍ እንዲሉ ሁሉም ተመጣጣኝ እውቀት እንዲኖረው የሚደረገው ጥረት በጥሩ መልኩ የሚያዝና ለቀጣይ በሌሎች ህዋሶችም መደገም የሚገባው ነው፡፡

ያሉትን በርካታ ውስብስብ ችግሮች በመረዳት አቅም የፈቀደውን መፍትሄ ማበጀት በህዋስ ደረጃ ሊበረታታ የሚገባው ድርጊት ነው፡፡

በየጊዜው የሚሰጡ አስተያየቶች እና በቀደምት አመራር የሚመራ ህዋስ መሆኑ ለተለያዩ አሰራሮች ችግር በማይፈጥር ሁኔታ እንዲንቀሳቀስ ጥረት ተደርጓል፡፡

ደጋፊ አመራሮች በየጊዜው በቅርበት በመከታተል ችግሮች በውይይት መፍታት በሚቻልበት ሁኔታ ድጋፍ ሲያደርጉ ስለነበር እንደመነሻ ጠቅመዋል፡፡

የነበሩ ማነቆዎች

- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ሂደት ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ ሁሉ ቢጋሩን በፍጥነት ለማግኘት ግን ማነቆ ሆኖ ቆይቷል

ከአመራሩ አንፃር የነበረው ማነቆ

- ይህ ነው የሚባል በአመራሩ ረገድ ክፍተት ባይኖርም በደራሽ ስራዎች መወጠር ታይቷል፡፡

ከህዋስ አባላት አንፃር የነበረው ማነቆ

- ይህነው የሚባል በህዋስ አባላቶች ረገድ ክፍተት ባይኖርም ሰዓት ማክበር ላይ የተወሰኑ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡

ከክትትልና ድጋፍ አንፃር የነበሩ ማነቆዎች

- ክትትልና ድጋፉን በተጠናከረ ሁኔታ ለማካሄድ በደራሽ ስራዎች መወጠር እና በተገቢው ግዜ አለ ማካሄድ

ክፍል ሶስት

የሚጠበቁ ውጤቶችና የተገኙ ተሞክሮዎች

የሚጠበቁ ውጤቶች

- በህዋሷ ውስጥ በመደራጀት ማህበራዊ፤ ፖሊቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ማቃለል መቻል
- በብልፅግናእሳቤውስጥበመሆንሰዋዊየሆኑተግባራትንበማከናወንርስበርስሰውመሰልእንቅስቃሴዎችንለሌሎችህዋሶችማስፋት
- ህዋሷ ማህበራዊ ሀላፊነቷን መወጣት ማስቻል
- በህዋሷ ስም ለህዳሴ ግድብ የራሰዋን ድረሻ መወጣት እንድትችል ማድረግ መቻል

የተገኙ ውጤቶች

- በህዋሷ ውስጥ በመደራጀት ማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ማቃለል ተችሏል
- በብልፅግ ና እሳቤ ውስጥ በመሆን ሰዋዊ የሆኑተግባራትን በማከናወን ርስበርስ ሰው መሰል እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ተችሏል
- አባላት በየጊዜው በመመልመል ብልፅግናን በአባላት ማጠናከር መቻሉ
- ህዋሷ ማህበራዊ ሀላፊነቷን መወጣት ችላለች፡፡ በዚህም የራሳቸው የሆነ ቁጠባ እንዲኖር በማድረግ እና ወደ አካባቢው በማስፋት፤ ችግረኞችን በመርዳት ብዙ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡

ውጤቶቹ የተገኙበት ሂደት

በየጊዜው በብልፅግና ፓርቲ እና በአስተዳደሩ ቀጥተኛ የሆነ ድጋፍ እንዲኖር በማድረግ በህዋሷ ውስጥም የተሻሉ አመራሮች በመገኘታቸው ውጦቶቹ ሊመጡ ችለዋል፡፡

ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ

እንደ ቦሌ ወረዳ 01 ሴቶች ሊግ ነባር ሞዴል ህዋስ እና መ/ድርጅት አዳዲስ የተቀላቀሉ አባላትንም ሆነ አዲስ የተመሠረቱ ህዋሳትን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ስራዎች የበለጠ እንዲሰሩ ያደርጋሉ በዚህም መሠረት ይለን ግንባር ቀደም መ/ድርጅት 3 ግንባር ቀደም አባላት 378 ግንባር ቀደም ህዋሳት 10ናቸው፡፡

መረጃ አያያዝና አጠቃቀም በተመለከተ

በመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ በተመለከተ በየጊዜው የሚከናወኑ ተግባራቶች በምስል እና በፁሁፍ የሚያዝበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ይህም ህዋሷ ውስጥ ያለው ሀሳብ ለአንድ አካባቢ ብቻ ሳይሆን ከዛም በላይ መድረስና መስፋት የሚችል ከብልፅግና እሳቤ ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ውጤቶቹን በማስመዝገብ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ችግሮች

- ተደራሽ ስራዎች መብዛት

የተወሰዱ መፍትሄዎች

- ስራዎችን አጣጥሞ መሄድ

ማጠቃለያ

በአንድ ቦታ ላይ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች ለሌላው በሚጠቅም ሁኔታ መስፋት አለባቸው፡፡ በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ ተግባራቶች በይበልጥ በህዋስ ውይይት ላይ ያለው ሂደት የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት አይነተኛ ሚና ስላለው እያንዳንዱ እንቅስቀሴ በማየት ለቀጣይ በሚጠቅም መልኩ ለሌላው ህዋስ መስፋት አለበት፡፡